# የሳክራሜንቶ መካነ ስላሴ 10 አመት ጉዞ






የድሮ አባቶች ሲተርቱ ታሪኩን ከስሩ ውህን ከጥሩ ይላሉ። ታድያ ዛሬን ላይ ቆመን ባለፈው የተፈጸመውን ተስፋ አስቀራጭና እልህ አስጨራሽ ጉዞ ስንመዝነው ስዎች ይጀምሩት እንጂ ፈጣርያችን ያሳከዋል የሚሉትን አባባል ያስታውሰናል። ለዚህም ነው ታሪክን የነበሩ ስዎች በጽሁፍ ማስፈርና ለአንባባቢ ወይንም ለአልነበሩ ስዎች ማስተላልፍ የሚጠበቅባቸው።
ታሪክም የአለፈውን ጊዜ መጥፎም ሆነ ጥሩ ስራ ለነበረው ያስታውሳል ለወዲፊቱ ደግሞ መስረታዊ ትምህርት ይሰጣል። በመሆኑም የሳክራሜንቶ መካነ ስላሴ ቤተክርስትያን አመሰራረትና ዛሬ የተደረሰበት ደረጃ ያሳለፈውን ረጅም ውጣ ውረድ ለምእመናንና ለአካባቢው ነዋሪዎች ማሳወቅና የነበረውን ውዥንብር ማስተካከል አስፈላጊሆኖ የተገኘው።
የቤተክርስትያኑ አመሰራረት ሰፋ ያለ ታሪክ አለው። ቤተክርስትያኑን ለመመስረት ደግሞ ብዙአስተዋጻኦ ያደረጉ ኢትዮጵያውያን አሉ። ይህን ሁሉ ለመዘርዝር ስለማየቻል የሚቀርበው ታሪክ በአጭሩ ነው። ለበቴክርስትያኑ ብዙ አስተዋጾ ያደረጉ ቢኖሩም በስም የምንጠቅሰው ግን በጣም ጥቂቱን ስማቸውን ባንጠቅስ ብንቀር ታሪኩን ለመንገር አያመችም ብለን ያመንበትን ብቻ ነው።
በግምት ካአስር አመት በፊት በስክራሜንቶ ከተማ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በጣም አነስተኛ ነበር። በተለይም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ቁጥር ደግሞ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። እነዚህ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸው የሚያስግድዳቸውን ነገሮች ለመፈጸም ወደ በርክሌይ ከተማ በመጓዝ በመድሃኔአለም ቤተክርስትያን ይገለገሉ ነበር።
የቤተክርስትያኑ መመስረት ምክንያት የሆነው ግን የአንድ ኦርቶዶክስ ተከታይ የሆነ ኢትዮጵያዊ ከዚህ አለም በሞት መለየቱ ነው። ለቀብሩ ስነስራት ለማድረግና የፍታት ስራት ለመፈጸም ከመድሃኔአለም ቤትክርስትያን ትብብር ተጠይቆ በወቅቱ የነበሩ ካህናት ግልጋሎት በሚገባ አከናወኑ።



በዚህም ወቅት
ነበር አንዱ መንፈሳዊ አባት
ወደሚያስተዛዝነው
ኢትዮጵያውያኖች ተጠግትው
የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን
መመስረት እንደሚያስፈልግ ሃሳብ
ያቅረቡት። በዛውም እለት
አስተባባሪ የሚሆኑ ሰዎች
አደራጅተው ከመድሃኔአለም
ቤተክርስትያንም አስፈላጊ ርዳታ
ኢንደሚያደርጉ ገለጹ። እኝህም
አባት የመካነ ስላሴ በተከርስትያን
አባት የሆኑት አቡነ መልከጸዲቅ
ናቸው።
በዚህ ወቅት አስተባባሪ ሆኖ የሰራው
ዶ/ር አያሌው ዓዳሙ ነበር።
ሌሎች
አብረው ያስተባበሩና በተለያዩ
ወቅት በቦርድ አባልነት ያገለገሉ
ግለሰቦች ስም ዝርዝር
በመጨረሻው ገጽ ላይ ተገልጽዋል።
የመካነ ስላሴ ቤተክርስትያን
በ1998 መስከረም ወር ላይ በግሪክ
ቤ/ክርስትያን ግልጋሎት ጀመረ።
ቢያንስ ለመጀመርያው 3 አመት
ግልጋሎት ይሰጥ የነበረው ቅዳሜ
ቀናት ነበር። ይህም የሆነው በሁለት
ምክንያቶች ነው። የመጀመርያው
ምክንያት ቅዳሴ የሚያካሂዱት
ካህናትና ዲያቆናት የሚገኙት
በመድሃኔአለም ቤትክርስትያን
ሲሆን ካሁኑና ዲያቅኑ ደግሞ
እሁድን ለመድሃኔአለም ግልጋሎት
መስጠት ስለነበረባቸው ነው።
ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ
ቤተክርስትንያችን የራሱ የሆነ ቦታ
ስሌለውና በተውሶ ቤተክርስትያን
ስለሚገለገል ነበር። በዚህ አጋጣሚ
ለረጅም ግዜ በነጻ እንድንገለገል
ለረዱን የአርሜንያን ኦርቶዶክስ
ቤተክርስትያን ምስጋና ለማቅረብ
እንወዳለን። በተጨማሪም በዚህም
ወቅት ያገለግሉን የነበሩት ካህናትን
ዲያቆናት እንዲሁ ምንም አይነት
ክፍያ ሳይጠይቁ በነጻ አገልግለዋል።
ለነዚህም የእግዚአብሄር አገልጋዮች
ዋጋቸውን እግዚአብሄር ይክፈላቸው።
በመጨረሻም እነዚህን ካህናትና
ዲያቆናት ለ2 ኣመት ከበርክሌይ
ሳክራሜንቶ በማመላለስ ያገለግሉ
የነበሩት ወ/ሮ ዘውዲቱ ፍስሃ የሚባሉ
ነበሩ። ለሳቸውም እንዲሁ የከበረ
ምስጋና ልናቀርብላቸው እንወዳለን።
በዚህ የአርሜንያን ቤተክርስትያን ወደ
አምስት አመት ያህል ከተገለገልን
በሗላ የመካነ ስላሴ ቤተክርስትያን
አነስተኛ የሆነች በ5001 ማርቲን
ሉተር ኪንግ መንገድ ላይ መቐርቐር
በቅታአል።ይችም ቤተክርስትያን
በጣም አነስተኛ ከመሆኑአ የተነሳ
አስፈላጊውን ግልጋሎት ለመስጠት
አስቸጋሪ ቢሆንም ሶስት አመታት
ያህል ተገልግልንበታል። ከዚህም
በሁዋላ እግዚአብሄር ምስገና ይግባውና
ዛሬ በመጠኑ ትልቅ የሆ ነ ካቴድራል
በዓባታችን ዓቡነ መልከጸዲቅ
አበረታችነት፤ በ አቶ ብንያም
ሙሉጌታ ቤተሰብና ምእመናን
የገንዘብ ድጋፍ ሊገዛ ተችሉአል።
ቤተክርስትያኑም
ትልቅበመሆኑ የተሸለ አገልግሎት
ምእመናኑ ሊያገኝ ችሉዋል።
ይህም ቤተክርስትያን የራሱ
የሆነ የመሰብሰብያ አዳራሽ፣
የህጻነት ትምህርት መሰጭያ፣
የካህናት መኖርያ ቦታ ያካተተ

በመሖኑ ምእማናን በፈለጉት
ሰኣት መንፈሳዊ ግልጋሎት
ለማግኘትና ከቤትክርትያን ኣባት
መንፈሳዊ ምክር ለማግኘት
ኣስችሎአል።
ይሕ የ10 ኣመት ጉዞ “ኣልጋ
በኣልጋ” ኤንደሚባለው
ኣለመሖኑና እንደውም ትልቅ
ፈተና የተፈታተነውና ረዥም
ጠመዝማዛ መንገድ
እንደገጠመው ልንገልጽ
እንወዳለን።

